# ልዑል እግዚአብሔር፡
## ከዘመነ ማርቆስ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋገሮ፡

የ፯ሺ፭፻፯ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ሰባተ)ኛውን ዓመት፥
የነጻነት ህልውናችንን በዓል፥

የ፪ሺ፯ (የኹለት ሽህ ሰባተ)ኛውን ዓመት፥
የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፣
የ፪ሺ፳፫ (የኹለት ሽህ ሃያ ሦስተ)ኛውን ዓመት፥
የእመቤታችን ድንግል ማርያምን
የልደታት በዓል ለማክበር ለበቃንበት፡

ለአዲሱ የ፪ሺ፯ (፳፻፯)
(ኹለት ሺህ ሰባት፥ ወይም፡ ሃያ መቶ ሰባት፥ ወይም፡ ዕሥራ ምዕት ወሰብዓቱ)
ዓመተ ምሕረት፥ መስከረም ፩ ቀን፣

ደግሞም፡
ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በዓላተ ግዝረት፥ በዓተ መቅደስና ስደት፥
እንዲሁም፡ ለዕፀ መስቀሉ የደመራና የበዓሉ ዕለት፥
ለእመቤታችንም፡ በዓለ ዕርገት፡

እንኳን፡ በያለንበት፡ በሰላም አደረሰን!

\+ \+ \+

# <u>ርእሰ አንቀጽ</u>

እግዚአብሔርን፥ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ልጆች በሚመለከት፡ በብሉዩ ኪዳን ነቢይ የተነገረው ቃል፡ በአዲሱ ኪዳን ባለራእይ፡ እንዲህ ተብሎ ተተርጉሟል፦ *"ዓለሙን ከመፍጠርህ በፊትም ኾነ፡ በኋላ፥ ምንጊዜም፡ ንጉሥ የኾንኸው፡ አንተ እግዚአብሔር፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብህ ለኾኑት፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ የሚያስፈልጋቸውን ሲሳይ ኹሉ ሰጠሃቸው፡፡ ስለዚህ፡ ያ፡ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት ዘንዶ፡ ኢትዮጵያን፡ ከነልጆቿ አጥለቅልቆ ለማስጠም፡ ወንዝን የሚያህል የማዕበል ውኃን፡ ከአፉ ተፍቶ፡ አፍስሶባት፡ ሊያጠፋት ባለመቻሉ፡ ቁጣው ነድዶ፡ 'የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፥ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን፥ ከዘርዋ የቀሩትን'፡ እኒህኑ፡ የቃል ኪዳን ልጆቿን ሊዋጋ፡ እነሆ፡ በባሕር አሸዋ ላይ ቆሟል፤ አንተም፡ እርሱን ቀጥቅጠህ፡ አዳንሃቸው፡፡"*

በዚህ የመለኮት ቃል፡ "ንጉሡ እግዚአብሔር"፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ "ኢትዮጵያ"፡ ንግሥት እናቱ፡ ድንግል ማርያም ናት፤ "'ከዘርዋ የቀሩት' ልጆቿ"፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸንተን የምንገኘው፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነን፡፡ "ከይሲ ዘንዶ"፡ ዲያብሎስ ነው፤ "ሰባት ራሶቹና አሥር ቀንዶቹ"፡ ቀድሞም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፡ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሡትና የሚነሡት፡ የእርሱ አገልጋዮችና መሣሪያዎች የኾኑት፡ ዛሬ፡ በዓለም ላይ በጥበባቸው፥ በገንዘባቸውና በኃይላቸው የሰፈኑት፡ ሰብአውያን መንግሥታት ናቸው፡፡

አዎን! የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከጥንት ጀምረው፡ እግዚአብሔርን አውቀውት፡ በሃይማኖት ቃል ኪዳን የተቀበሉት፡ *"ፈጣሪያችንና አምላካችን ነህ!"* ብለው ብቻ ሳይኾን፡ "ካህናችንና ንጉሣችንም ነህ!" ብለው መኾኑን ለማረጋገጥ፡ ከዚህ፡ ከብሉይ ኪዳኑ ቃል ጋር የሚጠቀስ፡ ተመሳሳይ የኾነ፡ የአዲሱ ኪዳን፡ የምሥራች ቃል አለ፤ ይህም፡ በካህኑ ኢትዮጵያዊ መልከ ጼዴቅ ሹመት፡የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ የታረደው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዲያብሎስን ድል መንሣቱ የታወጀበትና እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ሕዝባዊና ክህነታዊ፥ ብሔራዊና መንግሥታዊ ዓርማቸው አድርገው የኖሩት፡*"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ካህኑና ንጉሡ፡እግዚአብሔር ወልድ፥ እናቲቱና ንግሥቲቱ ድንግል ማርያም በሚመርዋት የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር ለሚተዳደሩት፡ *"ለዚች ሀገር ለኢትዮጵያና ለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላቸው፥ መብራቷም በጉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኾነ፡ ፀሓይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላቸው፡ አያስፈልጓቸውም!"* (መዝ. ፸፫ (፸፬)፥ ፲፪-፲፬፤ ራእ. ፳፥ ፳፤ ፲፪፥ ፩-፲፯፤ ፳፩፥ ፳፫፡፡)

ለእግዚአብሔር ይቅርና፡ በዚህ ዓለም፡ በግዘፍ ለምታበራው ፀሓይም እንኳ ቢኾን፡ ራሷ፡ የብርሃኑ ምንጭ ስለኾነች፥ በዚያ ብርሃኗም ስለተከበበች፡ ለራሷ፡ *"ትናንት፥ ዛሬና ነገ"* እንደሌለባት፡ ለማንም ግልጽ ነው፤ እንደርሷ ኹሉ፡ በጊዜና በሰዓታት፥ በቀንና በወራት፥ በዓመትና በዘመናት አቈጣጠር አማካይነት፡ እርሷ፡ ለሌሎቹ ፍጡራን የምታስገኛቸው፡ *"ትናንት፥ ዛሬና ነገ"*፡ **በኢትዮጵያ** እና **በኢትዮጵያ ልጆች ህልውና፡** ቦታ የላቸውም፡፡ የዓለሙ ብርሃንና ጨለማ፥ የጊዜው ደቂቃና ሰዓት፥ የዕለቱ መዓልትና ሌሊት፥ የወራቱ በጋና ክረምት የሚፈራረቁበት፡ የዓመቱ ዑደት (ዙረት) የሚያልቀው፥ እንደገናም የሚጀምረው፡ ለሥጋውያን፥ ለምድራውያንና ለዓለማውያን እንጂ፡ **ለኢትዮጵያ ልጆች** አይደለም፤ እኒህ **የኢትዮጵያ ልጆች**፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ በመወለዳቸው፡ የእግዚአብሔር ልጆች ኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስና እውነት፥ በልጁ የትንሣኤ ሕይወትና በእርሱ መንግሥታዊ ሥርዓት የሚኖሩ ናቸውና፡፡ (አሞ. ፱፥ ፯።)

በዳዊት መዝሙራት፡ *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"* የተባለችው ቅድስት አካልና ባሕርይ፡ **ድንግል ማርያም** ናት፤ ኢትዮጵያዊው ነቢይ ኤርምያስም፡ *"ኢትዮጵያዊ፡ መልኩን፥ ነብርም፡ ዝንጕርጕርነቱን ሊለውጥ ይችላልን?"* ብሎ፡ የተናገረለት፡ **ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡** እንዲህ ከኾነ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ለፍጹምነት ያበቁት **ኢትዮጵያዊነት፡** የእግዚአብሔር ሥራ ስለኾነ፡ <u>**እውነት**</u> ነው፤ ስለዚህ፡ <u>**ሃይማኖት**</u> ነው፤ ከዚህ የተነሣ፡ ሰዎች <u>**ሕይወት**</u> አድርገውት ይኖሩታል፡፡ እነዚህም፡ <u>**"የኢትዮጵያ ልጆች"**</u> (ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት) ይባላሉ፡፡ (መዝ. ፷፯ (፷፰)፥ ፴፩ ፡፡ ኤር. ፲፫፥ ፳፫፡፡)

እንግዲህ፡ **ኢትዮጵያዊነት፡** የእግዚአብሔር እውነት፥ ሃይማኖትና ሕይወት ስለኾነ፡ በግል፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ፥ በኅብረብሔርነትና በሕዝብነት፥ በአገርነትና በመንግሥትነት፥ ለወደፊትና ለዘለዓለሙም፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ በፍጹም ነጻነት፡ አንድ ኾነው የሚኖሩትና የሚኖሩበት ሥርዓት ኾኖ፡ እነሆ፡ ዘንድሮም፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና በእመቤታችን ድንግል ማርያም ረድኤት፡ ባለፈው ዘመን የወጣውን ዐዋጃቸውን ተከትሎ፡ <u>ለሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባተኛ ዓመት ዕድሜው በቅቷል፡፡</u>

+ + +

# የዓውደ ዓመቱ፡ ምሥራች መልእክት፡፡

በመስከረም ፩ ቀን፡ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ ምድር በከለላት፡ በኤዶም ገነት፡ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ፥ የቅዱሱ ኪዳን መጀመሪያ የኾነውንም፡ የቃል ኪዳን ሥርዓተ ጋብቻን፡ በእነርሱ መሥርቶ፡ ፍጥረቱን እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ፡ ሥልጣኑን በሰጣቸው ጊዜ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለግዙፉ ዓለም ተገለጠች! እርሷም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስከዛሬ የኖሩባት፥ ዛሬም እየኖሩባት ያሉ፥ በፍጻሜ ዘመንም፡ *"እናንተ የአባቴ ቡሩካን! ወደእኔ ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀችላችሁ ናትና፡ እንኳት ውረሷት!"* ተብለው፡ የጥንት ጠላቶቻቸው፡ ዲያብሎስና ሠራዊቱ፥ ኃጢኣትና ሞት ፈጽመው በተደመሰሱበት፥ "ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፈው፡ አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር በተተኩበት"፥ የቀደመው አሮጌና ብልሹ ሥርዓት ተሽሮና ተወግዶ፡ ዘለዓለማዊው የሙሽርነት ሥርዓት በሰፈነበት፡ አዲስ ሕይወት የሚኖሩባት ናት። (ራእ. ፳፩፥ ፩-፬፡፡)

የዚች መለኮታዊት መንግሥት ተቃዋሚ የኾነው እባቡ ዲያብሎስ፡ እስካኹን እንዳደረገውና ዛሬም እንደሚያደርገው ኹሉ፡ ረቂቅ የክፋት መርዙን፡ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች ህልውና ላይ ረጭቶ፡ ባደረሰው የጥፋት ርኵሰት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለው ከሚጠሩት፡ ኖኅንና ሓይከልን፥ መልከ-ጼዴቅንና ሳሌምን፥ አብርሃምንና ሣራን፥ ኬጡራንና ዮቶርን፥ ሙሴንና ሲጳራን፥ ዳዊትንና ቤትሳባን፥ ሰሎሞንንና ማክዳን ከመሰሉት ቅዱሳንና ቅዱሳት ወገኖች የተለዩት፡ የቃኤል ዘሮች፡ "የሰው ልጆች" ተብለው፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት፡ የየራሳቸው ምርጫ ያስከተለባቸውን፡ የመርገም ፍዳ ተቀባዮች ኾነው ኖሩ!

የተወሰነው፡ ይህ ዘመነ ኵነኔ ሲፈጸም፡ ቀድሞ፡ *በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ* ተብሎ የተነገረለት፥ ኋላም፡ *ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ* የተባለው፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ ዘላለማዊው ሊቀ ካህናትና እውነተኛው ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀድሞ፡ *ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር* ተብሎ፡ በነቢያት ከተነገረላት፥ ኋላም፡ "ወላዲተ አምላክ" ከኾነችው፥ እኛም ልጆቿ፡ "እምነ ጽዮን" እያልን ከምንጠራት፥ ከኢትዮጵያዊቷ እናት ንግሥታችንና ምድረ ርስት አገራችን፥ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንና የዘለዓለምም መቅደሳችን ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ **የዛሬ ፪ሺ፲ ዓመት ተወለደ፡፡**

ተወልዶም፡ በዲያብሎስ ረቂቅ ተንኰልና በሥጋ ባሕርይ ድክመት ምክንያት፡ በሰው ልጆች ላይ ተንሰራፍተው የኖሩትን፡ ክፋትንና መርገምን፥ ኃጢአትንና ሞትን በማስወገድ፡ በድል አድራጊነት፡ ዘመነ ምሕረትን፡ ለፍጥረቱ ኹሉ አጎናጸፈ፡፡ ይህን ፍጹም ጸጋ ለመቀበል "እምቢ!" ላሉት የሰው ልጆችም፡ *"እናንተ ርጉማን! ከእኔ ወግዱ! ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ፡ ወደዘለዓለም እሳት ኺዱ!"* የሚለውን የፍርድ ቃል፡ ለመጨረሻው ምጽአቱ አቆይቶላቸዋል፡፡

እነዚህ ዘመናት፡ ማለትም፡ ዘመነ ኵነኔውና ዘመነ ምሕረቱ ሲጠቃለሉ፡ ለቀረው ፍጥረት፡ ድምሩ፡ ፯ሺ፭፻፲ የኾነውን ዓመተ ዓለም፥ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ ፯ሺ፭፻፲ኛውን ዓመተ ኪዳን ያስገኛሉ፡፡

ስለዚህ፡ በዚች፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ **ኢትዮጵያ፡** እነሆ፡ **የ፯ሺ፭፻፲ኛውን** ዓመተ ልደቷንና የነጻነት ህልውናዋን፥ እንዲሁም የኪዳነ አዳምንና ሔዋንን፥ ከኹሉም በላይ፡ ቸሩ ፈጣሪዋ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደባትን ዕለት፥ የእርሷ፡ የቅድስት እናቱም፡ የልደት ቀን ከኾነችው፡ ከዚችው ዕለት ጋር አስተባብራ በማሰብ፡ በዓሏን፡ በዓቢይ ሓሤት ታከብራለች! ልጆቿ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ ይህን ታላቁን በዓላቸውን፡ ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በ፵ ቀኑ ወደቤተ መቅደስ እስከገባባት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ድረስ፡ እነሆ፡ በፋሲካ ሥርዓትና ዝግጅት፡ በያሉበት፡ በፍጹም ደስታ በማክበር፡ ለዚህ ላበቃቸው ፈጣሪያቸው፡ የተለመደ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡

*   *   *

ኋላ፡ ሐዋርያት፡ ዮሓንስን ሲያገኙት፡ "እመቤታችን እንደምን ኾነች?" አሉት፡፡ እርሱም፡ በዕፀ ሕይወትነቷ፡ ጥንት ወደነበረችበት፡ ወደገነት ተመልሳ፡ በዚያ፡ በጻድቃን ልጆቿ ነፍሳት መካከል ተገኝታ፡ በሰማያዊው የተድላ ዕረፍት ላይ እንዳለች አበሠራቸው፡፡

የቀሩት ሓዋርያት፡ "ዮሓንስ፡ ያን፡ በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የተፈጸመውን፡ የእመቤታችንን ፍልሰት አይቶ፡ እኛስ፡ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን!? አቤቱ÷ ለእኛም የቸርነትህን ድንቅ ሥራ ለማየት አብቃን!" ብለው፡ ወደፊት ቀጥሎ ባለው፡ በነሓሴ መባቻ (መግቢያ = ፩ ቀን)፡ በአንድነት ተሰባስበው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ የሱባኤ (የ፩ ሳምንት) ጾምና ጸሎት ጀመሩ፡፡

በኹለተኛው ሱባኤ ማብቂያ ዕለት፡ ማለትም፡ በነሓሴ ፲፬ ቀን እሑድ፡ እመቤታችንን፡ መልአኩ፡ ከገነት አምጥቶ፡ ለሓዋርያት ሰጣቸው፡፡ እነርሱም፡ ልመናቸው፡ በፈጣሪያቸው ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ስለተፈጸመላቸውና እመቤታችንን፡ በሕይወተ-ሥጋዋ እንዳለች፡ መልሰው ስላገኟት ደስ ብሏቸው፡ ፈጣሪያቸውን፡ በጸሎትና በዝማሬ አመሰገኑ፤ እርሷንም አወደሱ። እርሷም፡ እጅግ አጽናኝ የኾነውን፡ ሰማያዊዉን የሰላምና የፍቅር ድምፅዋን ካሰማቻቸው በኋላ፡ በዚያችው ዕለተ እሑድ ስላረፈች፡ ቅዱስ ሥጋዋን ወስደው፡ በመቃብርዋ አኖሩ።

እርሷም፡ በሦስተኛው ዕለት፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን፡ ማግሰኞ ተነሣች! የእመቤታችንን ትንሣኤ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ"÷ ማለትም፡ "እንደልጇ ትንሣኤ" ያሰኘው፡ ይህ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይታ የመነሣቷ ትንግርታዊ እውነታ ነው፡፡

አዎን! እንዲያ ባለ ፍልሰት፡ ወደአርያም ወጥታ፡ በብሔረ-ሕያዋን ከሚኖሩት፡ ከጻድቃን ነፍሳት ጋር፡ በገነት የቆየችው እመቤታችን፡ ነሓሴ ፲፬ ቀን፡ በዕለተ እሑድ፡ በመላእክት አጃቢነት ወደምድር ተመልሳ፡ በሓዋርያት መካከል፡ ከተገኘች በኋላ፡ ነፍሷ፡ ከሥጋዋ ተለየች። በዚህ ጊዜና ከዚህ ተከታትሎ የተፈጸመው ምሥጢር፡ ይህ ነው፡-

በአንድ በኩል፡ መለኮት፡ የትስብእት አካሉንና ባሕርዩን የነሣበትና የማሕፀን ማደሪያው ያደረገው ሥጋዋ፡ ከእሑድ እስከማግሰኞ፡ በመቃብር ዐርፎ ሣለ÷ በሌላው በኩል፡ ያው አንዱ መለኮት፡ እንደሥጋው ኹሉ፡ የትስብእት አካሉንና ባሕርዩን የነሣባትና የፅንሰት እውነታው ያደረጋት ነፍሷ ደግሞ፡ እንደልጇ ነፍስ፡ ብሔረ-ሙታን ወደኾነው፡ ወደሲዖል ወርዳ፡ በልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሚ ትንሣኤ የተገኘው ምሥራች፡ በእርሷ ተከታይነት እየቀጠለ መኼዱን፡ በዚያ ለታሠሩት ኃጥኣን፡ የንስሓ ጸጋን፡ ካበሠረችላቸው በኋላ፡ በመቃብር ከቆየው ሥጋዋ ጋር፡ በሦስተኛው ቀን ተዋሕዳ፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች!

በዚህም፡ ያ፡ ቀደም ብሎ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ፡ መሞትና መቀበር÷ በነፍስ ደግሞ፡ ወደሲዖል መውረድና ለነፍሳት መስበክ÷ በመጨረሻም፡ መነሣትና ማረግ፡ ተፈጽሞ የታየው መለኮታዊ ትንግርት፡ እነሆ፡ በቅድስት እናቱ፡ በድንግል ማርያም የቅድስና ሕይወት፡ እንደገና ተከሠተ! በእውንም ተረጋገጠ፡፡

ይህም፡ "መለኮት የተዋሓዳት፡ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በመስቀል ላይ፡ ራቁቱን ከተዘረጋው ሥጋዋ ተለይታ፡ ያሙት ነፍሳትን፡ ነጻ ልታወጣ፡ ወደሲዖል ወርዳ ሣለች፡ ያ በመስቀል ላይ ቀርቶ የነበረው፡ መለኮት የተዋሓደው ሥጋ ደግሞ፡ በመቃብር ዐርፎ፡ ከቆየ በኋላ፡ በሦስተኛው ቀን፡ እሑድ፡ ሥጋውና ነፍሱ እንደገና ተዋሕደው፡ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ" ማለት ነው፡፡

\+ \+ \+

ይህ ኹሉ ሲኾን፣ ማለትም፡ በመጀመሪያው የሓዋርያት ሱባኤ ጊዜ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም፡፡ ለሓዋርያት በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ሥልጣን፡ እርሱም፡ እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት ዘግይቶ፡ በዚያ እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሓዋርያት ሲመጣ፡ እመቤታችንን፡ ከሙታን ተለይታ ከተነሣች፡ ከአርባ ቀን በኋላ፡ ስታርግ አገኛት፡፡

ያችም ዕለት፡ እንደልጇ ትንሣኤ፡ በ፫ኛው ቀን የኾነው ትንሣኤዋ ብቻ ሳይኾን፡ ዕርገቷም፡ እንደልጇ ዕርገት፡ በ፵ኛው ቀን የተፈጸመባት፡ መስከረም ፳፩ ቀን፡ እሑድ ነበረች።

ቶማስ፡ ባልጠበቀው በዚህ ትርኢት፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታውከበት፡ "ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቹ ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ፡ ለዚያ ዕድል ሳልበቃ ቀረሁ፤ አኹንም፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ያንቺን ትንሣኤ ቀድመው ሲያዩ፡ ይኸው፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ።" ብሎ ማዘኑን ገለጸላት።

እመቤታችንም፡ "አይዞህ! አትዘን፤ እኒያ ወንድሞችህ፡ ኹሉም፡ ትንሣኤዬን፥ ዕርገቴንም አላዩም፤ አንተ ግን፡ ፈጣሪዬ ባወቀውና ባዘጋጀው የቸርነት ሥራው፡ ታድለሃል፤ ኹለቱንም አይተሃልና። አኹንም፡ ኼደህ፡ 'ተነሣች! ዐረገች!' ብለህ ንገራቸው!" ብላ፡ ተገንዛበት የነበረውን ሰበን (ሸማ) ሰጥታ፡ ከበረከቷ ጋር ሰደደችው።

ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባኤና በጉባኤ የሰነበቱትን ሐዋርያትን ሲገናኛቸው፡ "ኧረ! የእመቤታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው።

እነርሱም፡ "ኹለተኛውን ሱባኤያችንን እንዳበቃን፡ እመቤታችን፡ በዚያው፡ ተለይታን በነበረችበት ኹለንተናዋ፡ ወደእኛ ተመልሳ መጥታልን፡ ተቀብለናትና አግኝተናት፥ አነጋግረናትና እንደቀድሞው፡ በመካከላችን ተቀምጣ፡ ሰማያዊ የኾነ፡ የሰላምና የፍቅር ድምፅዋን እየሰማን ቆይተን ሣለን፡ በዚያችው ዕለት፡ የመጨረሻ በረከቷን አሳድራብን፡ ስላረፈች፡ ሥጋዋን፡ እንደጌታችን ልጇ፡ ወስደን፡ በጌቴሴማኒ መቃብር አኖርን!" አሉት።

"መቼ?" አላቸው።

"በነሓሴ መባቻ፡ ሱባኤ ገብተን፡ በ፲፬ኛው ቀን!" አሉት።

እርሱም፡ በመገረም፡ "ፍልሰት በጥር፥ በነሓሴ መቃብር! ኧረ ተዉ! ይህ ነገር፡ አይመስለኝም!" አላቸው።

ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስም፡ "አንተ እንጇ፡ ልማድህ ነው! አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም፤ አንተ እየተጠራጠርህ፡ ሰውን ኹሉ፡ ስታጠራጥር ትኖራለህ፤ አኹንም፡ እውነቱን ልታውቅ ከወደድህ፡ ና እይ!" አለውና ከወንድሞቹ ጋር ወደመቃብሩ አመራ።

ቶማስም፡ የያዘውን ያውቃልና፡ ጸጥ ብሎ ሰምቷቸው፡ ተከተላቸው።

ከዚህ በኋላ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ተቆጥቶ ኼዶ፡ መቃብሩን ቢከፍተው፡ አጣት፤ እርሱም፥ አብረውት የነበሩት፡ የቀሩት ሐዋርያትም ደንግጠው በያሉበት ቆሙ።

በዚህ ጊዜ፡ ቶማስ፡ "'አታምኑኝም!' ብዬ ነው እንጇ፡ እመቤታችንስ፡ ደስ ይበላችሁ! ተነሥታለች! ዐርጋለች!" አላቸው።

ከእርሷ ያገኘውን፥ በእነርሱ፡ በሐዋርያት እጅ የተገነዘችበትንም ሰበን ሰጣቸው።

ሐዋርያት፡ ያን በማየታቸው፡ ደስ አላቸው፤ ሰበኑንም፡ ለበረከት ተካፈሉት።

\+ + +

ይህ በኾነ፡ ልክ፡ በዓመቱ፡ የቀሩት ሐዋርያት፡ "ቶማስ፡ ትንሣኤሽን፥ ዕርገትሽንም አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? አቤቱ፡ እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተህ፡ አሳየን!" ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛውን፡ የሱባኤ ጾምና ጸሎታቸውን፡ ነሓሴ ፩ ቀን፡ በአንድነት ጀመሩ።

ነሓሴ ፲፬ ቀን፡ ኹለት ሱባኤን ጨርሰው፡ በሦስተኛው ዕለት፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደጽርሓ አርያም ወስዷቸው፡ በዚያ፡ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ቄስ፥ ቅድስት እናቱን፡ እመቤታችንን፡ ድንግል ማርያምን፡ መንበር፥ ቅዱስ ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፥ ቅዱስ እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ፡ ቆርቦ፥ እርሷንም፥ እነርሱንም፡ አቍርቧቸዋል።

